# ምዕራፍ አምስት

# ቀና አመለካከት

**የምዕራፉ ዓበይት ዓላማዎች፡-** ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ✓ ስለ ቀና አመለካከት ጠቀሜታ ተገንዝባችሁ ትገልጻላችሁ፡፡
- ✓ ሐረጋትን በዓይነታቸው ለይታችሁ ትመድባላችሁ፡፡
- ✓ ተራና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ✓ ከተለያዩ ምንጮች የምታገኟቸውን መረጃዎች በሚመለከት ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ✓ አመዛዛኝ ድርሰት ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ለምሣሌያዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ መልእክት ያላቸውን ምሳሌያዊ አነጋገሮች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ እንቶኔን፣ ምፀትንና ግነት ዘይቤን በጽሑፋችሁና በንግግራችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

© MoE, FDRE
Not to be reproduced

## ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች አንድ ሰው ቀና አመለካከት አለው ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. ቀና አመለካከት ያላቸው ሰዎች በህይወታቸው ምን ጠቀሜታ የሚያገኙ ይመስላችኋል? የሌላቸውስ?
3. በሰዎች ዘንድ ቀና አመለካከት መኖር ሀገራዊ ፋይዳው ምንድን ነው?

## "ምንም የማይቻል ነገር የለም!"

"ምንም የማይቻል ነገር የለም!"

"ይተው እንጂ፣ ዶክተር!" ትሉ ይሆናል፡፡ "እርስዎ የተማሩ ሰው ነዎት፡፡ እንዴት 'ምንም የማይቻል ነገር የለም!' ይላሉ? አእምሮዎን ስተዋል እንዴ?!" ልትሉም ትችላላችሁ፡፡

"አይቻልም!" የሚለውን ቃል ከአእምሮዬ ውስጥ ካስወጣሁት ከረምኩ፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ በብዙ ምክንያቶች ከቃሉ ጋር የነበረኝን ቁርኝት አቋርጫለሁ፡፡

"አይቻልም" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ በጥቅም ላይ የሚውለው ደንታ ቢስ በሆነ፣ በተስፋ መቁረጥና ፍሬ በሌለው ሁኔታ ነው፡፡ እና በፍጹም አእምሮዬን አልሳትኩም፡፡ እጄን ለእነዚህ ከንቱ ስሜቶች አልሰጥም፡፡ ስለዚህም "አይቻልም" የሚለውን ቃል ከእስር አውጥቼ ፈታሁት!

በምድር ላይ እጅግ አደገኛው አስተሳሰብ የጨለምተኛነት አስተሳሰብ ነው፡፡ ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያለው ሰው ከዚህ ቀደም ተሞክሮ ያልተሳካ አንድ ተግባር የሚያውቅ ከሆነ ያ ተግባር ያልተሳካው መጀመሪያውኑ "የማይቻል ስለሆነ ነው" ብሎ አምኖ እናንተንም ያሳምናችኋል፡፡ ዓለም በሙሉ እውነተኛ ያልሆነች፣ ያልተጨበጠች፣ አስቸጋሪ፣ የማትታሰብ እና የማትቻል እንደሆነች ይሰብካችኋል፡፡ እናም ይህ ዓይነቱ ሰው እድገትን ይገድባል፤ ልማትን ያጨናግፋል፣ ፈጠራን ያቀጭጫል፤ ጠልቆ ማሰብን ይገታል፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

**ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ በማድረግ ከላይ ባነበባችኋቸው አንቀጾች ውስጥ ያገኛችኋቸውን ነጥቦች ለመምህራችሁ ተናገሩ፤ በሚቀጥሉት የምንባቡ አንቀጾች ውስጥ ሊነሱ ይችላሉ የምትሏቸውን ሐሳቦችም ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡**

ከዚህ በተቃራኒ ቀናው አስተሳሰብ የ“ይቻላል” አስተሳሰብ ነው፡፡ የዚህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለው ሰው አዲስ ሀሳብ ሲያጋጥመው የአሸናፊነት ስሜት በውስጡ ስለሚሰማው በገጠመው እድል የሚደሰት ነው፡፡ ለአሮጌ ችግሮች የአዲሱን ትውልድ መፍትሔዎች በመጠቀም አዲስ ታሪክ ለመሥራት ባገኘው አጋጣሚ ይነቃቃል፡፡ የማይታለፉ የሚመስሉ እንቅፋቶች የሚፈቱበት አንድ መንገድ አለ ብሎ ስለሚያምንም በልበ ሙሉነት ወደ ተግባር ይገባል፡፡ ሁሌም ለስኬታማ ጉዞው ስንቅ የሚያደርገው “ይቻላል!” የሚለውን ቃል ነው፡፡

- “የልብ ቀዶ ህክምና?! በፍጹም አይቻልም!”
- “ሰውን ጨረቃ ላይ ማስቀመጥ?! ተው እንጂ! በፍጹም አይቻልም!”
- “ከአንድ የእግር ኳስ ሜዳ በላይ ቁመት ያለው ህንፃ መገንባትና የመሬት መንቀጥቀጥን እንዲቋቋም ማድረግ?! በፍጹም አይቻልም!”

አስተውሉ! እነዚህ ሁሉ ተችለዋል፡፡ “አይቻልም” ሲሉ የነበሩትም በሀፍረት አንገታቸውን ደፍተዋል፡፡

እናንተ የዚህ ዘመን ባለአደራዎች፤ ራሳችሁን ከክፉ አስተሳሰብ አርቁ! በቀና አስተሳሰብ አንጹ! ስኬታማ ለመሆን ስንቃችሁ “ይቻላል!” የሚለው ቃል ይሁን፡፡

*(ምንጭ፡- በሮበርት ኤች. ሹለር ተጽፎ በማኀሌት ጥላሁን ከተተረጎመው “አመለካከትን በመለወጥ ሕይወትን መለወጥ የሚስችሉ ታላላቅ መንገዶች” ከሚለው መፅሐፍ ለማስተማር እንዲያመች ተደርጎ የተወሰደ (48-50)፡፡)*

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## ክፍል አንድ፣ አንብቦ መረዳት

**፩. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በጥሞና በማንበብ ትክክል የሆኑትን ‘እውነት’ ስህተት የሆኑትን ደግሞ ‘ሐሰት’ በማለት መልሱ፡፡**

1. ደንታ ቢስ የሆኑ ሰዎች የ “ይቻላል!” መርህ ተከታዮች ናቸው፡፡
2. የጽሑፉ አቅራቢ በዚህ ምድር ላይ የማይቻል ነገር የለም የሚል አቋም አላቸው፡፡
3. የሚቻሉ ነገሮችን “አይቻልም!” ሲሉ የነበሩ ሁሉ ትንቢታቸው ሰምሮላቸዋል፡፡
4. እስካለንበት ዘመን ድረስ የሰውን ልጅ ጨረቃ ላይ ማሳረፍ አልተቻለም፡፡
5. የስኬታማ ህይወት ተቋዳሾች ዓለምን በብሩህ መልኩ የሚቀበሉ ናቸው፡፡

**፪. የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃላት ላይ በመፈለግ ጻፉ፡፡**

| | |
|---|---|
| 1. ተቆራኘ | 6. መፍትሔ |
| 2. ተስፋ | 7. ስንቅ |
| 3. ስኬት | 8. ማነፅ |
| 4. ሰበከ | 9. ቀና |
| 5. ተጨናገፈ | 10. ጥልቅ |

**፫. የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ክፍል ውስጥ ጥንድ በመሆን ተነጋገሩባቸው፤ በመቀጠልም በጋራ ተወያዩበት፡፡**

1. በምንባቡ ከቀረቡት አስተሳሰቦች መካከል በህይወታችን ልንከተለው የሚገባው አስተሳሰብ የትኛውን ነው? ለምን? አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡
2. "አዲስ ታሪክ ለመሥራት ይነቃቃል" የተባለው ትውልድ የትኛውን አስተሳሰብ የሚከተለው ነው? ለምንስ ስኬታማ ይሆናል ተባለ?
3. ጨለምተኛ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ህይወታቸውን በምን ዓይነት መንገድ ማስተካከልና መምራት እንዳለባቸው ያላችሁን ሀሳብ ተናገሩ፡፡

© MoE, FDRE, Not to be reproduced

© MoE, FDR
Not to be rep

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

፩. በቡድን ሆናችሁ "ቀና አመለካከት" በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ አዘጋጁና በክፍሉ ፊት በምትወክሉት አቅራቢ አማካይነት አቅርቡ፡፡

፪. በቡድን በመሆን ቀና አመለካከት ያለውን ማህበራዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለክፍሉ አጋሩ፡፡

፫. በአካባቢያችሁ ከሚደረጉ የአዋቂ ሰዎች ህዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ያገኟችኋቸውን ፍሬ ሐሳቦች በማስታወሻ ይዛችሁ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- መጻፍ

***ታማሪዎች!* ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሠረት አድርጉና ቀና አመለካከት ያላቸውንና የሌላቸውን ሰዎች በማነጻጸር ከሁለት ገጽ ባልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

### አመዛዛኝ ድርሰት

የድርሰት ዓይነቶችን በተመለከተ የቋንቋ ሊቃውንት አንድ ዓይነት አመለካከት የላቸውም፡፡ አንዳንዶች ስድስት፣ ሌሎች አራት፣ ሌሎች ደግሞ ሦስት ናቸው ይላሉ፡፡ በዚህ ምዕራፍ የምናየው በሁሉም ምድብ ውስጥ የማይጠፋውን አመዛዛኝ ድርሰትን ነው፡፡

አመዛዛኝ ድርሰት አከራካሪ ስለሆኑ ጉዳዮች የሚጽፍ፣ አንባቢውን /አድማጩን/ የአንድን ጉዳይ እውነትነት ወይም ሐሰትነት ለማሳመን የሚጥር፤ ደራሲው /ጸሐፊው/ ለአንድ ወገን ቆሞ አንድን ጉዳይ በአንድ መልኩ ብቻ በመቃወም ወይም በመደገፍ ሊጽፍ የሚችልበት፣ ወይም ለሁለቱም አከራካሪ ሐሳቦች የቆመ በመምሰል ጉዳዩን በመደገፍና በመቃወም አቅርቦ በመጨረሻም ማስረጃው ያደላበትን አጠናክሮ በመተቸት አንዱን በማጠናከር ወደ አንድ ውሳኔ የሚደርስበትና ለማሳመን የሚጥርበት የድርሰት ዓይነት ነው፡፡

**የአመዛዛኝ ድርሰት ምሳሌ፡-**

ብዙ የሥነ-ትምህርት ተመራማሪዎች የመማር ማስተማር ዘዴ ትምህርት "ሳይንስ" ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ "አርት" ነው ይሉታል። "አርት" ነው የሚሉት ተመራማሪዎች የመማር ማስተማር ዘዴ ምንም ህግ የለውም ይላሉ። "የተማረ ያስተምር" እንደሚሉት ዓይነት ነው።

ጥሩ አስተማሪነት የሚመነጨው ከሰውየው ችሎታ እንጂ ከሚያገኘው ሥልጠና አይደለም ይሉናል። ለአስተማሪ የሚያስፈልገው የሚስተምረውን የትምህርት ዓይነት ጠንቅቆ ማወቅ ነው፣ በማለት በአጽንኦት ይከራከራሉ።

"ሳይንስ" ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ህጐች አሉት። አስተማሪው ህጐችን ጠንቅቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በክህሎትና በአመለካከቱም በኩል ያሉትን ህጐች የሚያንጸባርቅ ባህሪይ ማሳየት የሚችል መሆን አለበት ነው የሚሉት። በዚህም መሠረት መምህር የሚሆን ሁሉ በሥነ ትምህርት ሳይንስ የሰለጠነ መሆን አለበት ይላሉ።

ሰውን ካስተማርከው ይማራል፣ የሚል የክርክር መነሻ ያላቸው ሰዎች ይኖራሉ። ማስተማር ሌላ ጉዳይ ነው፤ መማር ደግሞ የተለየ ነው፤ የሚሉ ሰዎች ደግሞ ሞልተዋል። ታዲያ ማስተማር መማርን እንዲያስከትል ከተፈለገ የመማር ማስተማርን ህጐች ጠንቅቆ ማወቅ አያስፈልገንም? መማርን የሚያስከትሉ ነገሮችን ማወቅ ማለት ደግሞ መንስኤና ውጤትን ማወቅ ማለት ነው። ስለዚህ እነዚህ ነገሮች ከስነ-ትምህርት ሳይንስ የሚገኙ ስለሆኑ መምህራን የስነ-ትምህርት ሳይንስ ትምህርትን በሚገባ ማጥናት ይኖርባቸዋል።

*ከመፅሔተ ትምህርት ክቅፅ 1. ቁጥር 1 ላይ የተወሠደ*

## ክፍል አራት፡- ሰዋስው

**፩. የሐረጋት ምስረታ ህግጋትን በመመርኮዝ “ምንም የማይቻል ነገር የለም” በሚለው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ሐረጋትን በተሰጠው ሠንጠረዥ ውስጥ በየዓይነታቸው መድቧቸው።**

| | ግሳዊ ሐረግ | ስማዊ ሐረግ | ቅጽላዊ ሐረግ | ተውሳከ ግሣዊ ሐረግ | መስተዋድዳዊ ሐረግ |
|---|---|---|---|---|---|
| **ምሳሌ** | … የማይቻል ነገር የለም፡፡<br>ሀ. ________<br>ለ. ________<br>ሐ. ________<br>መ. ________ | የተማሩ <u>ሰው</u>፣ | ምንም <u>የማይቻል</u>፣ | አሁኑኑ <u>ቶሎ</u>፣ | <u>ከ</u>አእምሮየ <u>ውስጥ</u> |

**፪. ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት ከተሰጣችሁ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ተራ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** በፍጥነት እየነዳ ወደ ሥራ ሲሄድ፣ ከጭነት መኪና ጋር ተጋጭቶ ክፉኛ ቆሰለ፡፡ (ውስብስብ ዓረፍተ ነገር)

**መልስ፡-** የተመሠረቱ ተራ ዓረፍተ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. በፍጥነት ነዳ፡፡
2. ወደ ሥራ ሄደ፡፡
3. ከጭነት መኪና ጋር ተጋጨ፡፡
4. ክፉኛ ቆሰለ፡፡

1. መክሰስህን ቶሎ በልተህ ጥናትህን ጀምር፡፡
2. ወደ ፎቅ ከወጣህ በኋላ ወደ ቀኝ ታጠፍና ሁለተኛውን በር አንኳኳ፡፡
3. ወንድሟ ወደ ውጭ ሀገር በመሄዱ ከጓደኛዋ ጋር ሆና ምርር ብላ አለቀሰች፡፡
4. መምህርህ የቤት ሥራህን ባለመሥራትህ የፈለጉትን ያህል ቢቆጡህ ቂም መያዝ የለብህም፡፡
5. መንግሥት የሕዝቡን ችግር በማየት የመፍትሔ ሐሳብ አቅርቧል፡፡

**፫. ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት ከተሰጣችሁ ተራ ዓረፍተ ነገሮች ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ተራ ዓረፍተ ነገሮች
1) መሐመድ ጎበዝ ልጅ ነው፡፡
2) ቀልድ ያበዛል፡፡

የተመሠረቱት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች
ሀ) መሐመድ ጎበዝ ልጅ ቢሆንም፣ ቀልድ ያበዛል፡፡
ለ) መሐመድ ጎበዝ ልጅ ነው፤ ቢሆንም ቀልድ ያበዛል፡፡

© MoE, FDRE Not to be republished

1. ሀ. ሐሳቡ አይገባኝም፡፡ ለ. ከማጥናት አልቆጠብም ፡፡
2. ሀ. አዲሱን ኮት አገላበጠው፡፡
   ለ. አዲሱን ኮት አየው፡፡
   ሐ. አዲሱን ኮት ገዛው፡፡
3. ሀ. ፊቱን ታጠበ፡፡ ሐ. መማሪያዎቹን ያዘ፡፡
   ለ. ቁርሱን በላ መ. ወደ ት/ቤት ሄደ፡፡
3. ሀ. በዚህ ክፍል ውስጥ ጥቂት ሰነፎች አሉ፡፡
   ለ. አብዛኞቹ ግን ዓላማቸውን አይስቱም፡፡
4. ሀ. ከበደ መጣ፡፡ ለ. በጣም አስገረመኝ፡፡

፬. ስለተራና ውስብስብ አረፍተ ነገሮች የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ አምስት ተራ እንዲሁም አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ስነጽሑፍ

፩. በምሣሌው መሠረት ለሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተስማሚ የሚሆኑትን በሳጥን ከቀረቡት ውስጥ በመምረጥ ባዶ ቦታው ላይ አስፍሩ፡፡

ምሳሌ፡-

1. ሺህ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ = ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ፡፡

ሀ. "ባልበላ ጭሬ ላፍስሰው" አለች፣ ዶሮ፡፡
ለ. ተልባ ቢንጫጫ ባንድ ሙቀጫ፡፡
ሐ. ሰርገኞች መጡ ብቅል አስጡ፡፡
መ. ችኩል አደንጓሬ ሳይበስት ሆድ ያማል፡፡
ሠ. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ፡፡

2. ዝናብ ሲያባራ ወደ ዋሻ = ____________________
3. ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ = ____________________



© MoE, FDRE, Not to be reproduced

4. “እኔ ከሞትሁ ሥርዶ አይብቀል” አለች ፣ አህያ = ____________
5. የቸኮለች አፍስሳ ለቀመች = ____________

**፪. በፍች የሚመሳሰሉ ሁለት ሁለት ምሣሌያዊ አነጋገሮች በመፈለግ በደብተራችሁ ላይ በማስፈር ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

## ዘይቤ

1. **እንቶኔ ዘይቤ፡-** በአጠገብ የሌለን ሰው ወይም ሰው ያልሆነ ነገር በቅርብ እንዳለ፣ እንደሚሰማንና መልስ እንደሚሰጠን አድርገን በመቁጠር መልዕክት የምናስተላልፍበት የዘይቤ ዓይነት ነው፡፡

   **ምሳሌ፡-** 1. እናቴ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ፣
   የሠራልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፡፡
   2. ተናገር አንተ ሐውልት!

**አስተውሉ፡-** በሁለቱም ምሳሌዎች የምናናግራቸው ግዑዛን በሁለተኛ መደብነት እንደተቀመጡ አስተውሉ፡፡ ያናገርናቸው “አንተ”፣ “አንቺ” እያልን ነው፡፡

2. **ምፀት ዘይቤ፡-** ከምንናገረው ቀጥተኛ ንግግር በተቃራኒው ሐሳባችንን የምናቀርብበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘይቤ በምክር ስድብን፣ በሙገሣ ማዋረድን፣ በሣቅ ሐዘንን ወዘተ. በጎንዮሽ አነጋገር የምንገልጽበት ዘይቤ ነው፡፡

   **ምሳሌ፡-** አጭሩን ሰው ሎጋ ከሲታውን ዱባ፣
   እጅግ ቀርፋፋውን ሰው ‹ጀት›

3. **ግነት ዘይቤ፡-** አንድን ነገር ካለው ነባራዊ ይዘት በማጋነን የሚያቀርብ ረቂቁን የሚያገዝፍ እና የሚያጎላ የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   **ምሳሌ፡-** ዝሆን የሚያህል ቁንጫ ገደልኩ፡፡
   የጨረቃዋ ብርሀን ጤፍ ያስለቅማል፡፡

**፫. ከፍ ሲል በተማራችሁት መሠረት በእያንዳንዱ የዘይቤ ዓይነት ሥር ሦስት፣ ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን ሠርታችሁ በክፍል ውስጥ ተወያዩበት፡፡**

1. እንቶኔ ዘይቤ፡- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________
2. ምፀት ዘይቤ፡- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________
3. ግነት ዘይቤ፡- ሀ. ____________ ለ. ____________ ሐ. ____________



© MoE, FDRE Not to be reproduced

© MoE, FDR
Not to be rep

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ይህ ምዕራፍ የቋንቋ አጠቃቀምን፣ ሰዋስውና ስነ ጽሑፍን በሚገባ ያየንበት ምዕራፍ ነው፡፡ በምዕራፉ ውስጥ ሐረጋትን በዓይነታቸው ለይተን በማውጣት ማየት ችለናል፡፡ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን ከተራ ዓረፍተ ነገሮች እንዴት እንደምንለይ፣ ከውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተራ ዓረፍተ ነገሮችን እንዴት እንደምንመሰርትና ከተራዎቹ ዓረፍተ ነገሮች ደግሞ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን እንዴት እንደምንመሰርት ተረድተን ተግባራዊም አድርገናል፡፡ ለተሰጡን ምሳሌያዊ አነጋገሮችም ተመሳሳይ የሆኑ ምሣሌያዊ አነጋገሮችን ፈልገናል፡፡ የተሰጡትንም ዘይቤያዊ አነጋገሮች ምንነት ተረድተን ዓረፍተ ነገሮችን በሚገባ መስርተንባቸዋል፡፡ በጥቅሉ የአጻጻፍ ስልታችን ሻል ባለ የቋንቋ አጠቃቀም ለማዳበርና ሰዋስዋዊ የሆኑ ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም ድርሰት ለመጻፍ ጥረት ያደረግንበት ምዕራፍ ነበር፡፡

## የክለሣ ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ተደባልቀው የተቀመጡት የተለያዩ አምስት ዓይነት ሐረጋት ናቸው፡፡ በመሆኑም ከፊት ለፊታቸው በሚሰጣችሁ ባዶ ቦታ ላይ ግሣዊ ሐረግ፣ ስማዊ ሐረግ፣ ተውሳከ ግሣዊ ሐረግ፣ መስተዋድዳዊ ሐረግ ወይም ቅጽላዊ ሐረግ በማለት መልስ ስጡ፡፡

ጥቁር ድንጋይ ______________ አሁኑኑ በፍጥነት______________

እጅግ በጣም ጥቁር______________ ከዛፉ ሥር______________

ቆሎ የሚያኳርስ ፍቅር______________ እስከዳር______________

አበባው አበበ______________

፪. የሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች በምን ዓይነት አውድ እንደሚነገሩ ተወያዩባቸው፡፡

1. ሌባ ሳመሉ ዳቦ ይልሳል፡፡______________
2. ሰው ለሰው መድሃኒቱ ነው፡፡______________
3. አባብ ያዬ በልጥ በረየ፡፡______________

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቧል፡፡ በዚህ መሠረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(x) ምልክት በማድረግ ቅፁን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሣከሪያ ነጥብ | √ | ? | x |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ስለ ቀና አመለካከት የቀረበውን ምንባብ ይዘት መግለፅ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 2. | ሐረጋትን በዓይነታቸው በመለየት መመደብ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 3. | ውስብስብና ተራ ዓረፍተነገሮች እመሰርታለሁ፡፡ | | | |
| 4. | ማስታወሻ የመያዝ ስልትን በመከተል የተለያዩ ንግግሮችን በማዳመጥ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ እይዛለሁ፡፡ | | | |
| 5. | አመዛዛኝ ድርሰት መጻፍ እችላለሁ፡፡ | | | |
| 6. | ለተለያዩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተመሳሳይ ፍች ያላቸውን ምሳሌያዊ አነገጋገሮች እሰጣለሁ፡፡ | | | |
| 7. | የእንቶኔ፣ የምፀትና ግነት ዘይቤዎችን ምንነት ተረድቻለሁ፡፡ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ (?) እና የ(x) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡



© MoE, FDRE Not to be reproduced